1) መልካም አመራረት ስርዓት ቁጥጥር ላይ የሚመደቡ ሁለም ተቆጣጣሪዎች በፋርማሲ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ መሆን አለባቸዉ፡፡ ሆኖም ሌሎች ባለሙያዎች (ኬሚስት ፣ ማይክሮባዮልጂስት እና ባዮሎጂስት) አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት፣ የስራ ልምድ እና ብቃት እንዳላቸው ሲረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ በተቆጣጣሪነት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡	

2)

ለም ተቆጣጣሪዎች በመልካም አመራረት ቁጥጥር በተቆጣጣሪነት ለመመደብ ብቃታቸዉ የተረጋገጠ መሆን ያለባቸዉ ሲሆን የተደራጀ የላቀ የመልካም አመራረት ስርዓት ስልጠና ያገኙእና አግባብነት ባለው ፈተና አዘጋጅ አካል የተዘጋጀ የምዘና ፈተና የወሰዱ መሆን አለበቸው፡፡ እያንዳንዱ እፊዩ ተቆጣጣሪ ለመጀመሪያ ግዜ ስራው ላይ ሲሳተፍ ቢያንስ በፈተናው 60 ከመቶ የማለፊያ ነጥብ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡

3)

ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ፈተና ዝግጅት፣ ፈተና ሲሰጥና የተቆጣጣሪዎች ግምገማ ሲካሄድ በመድኃኒት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ክትትል ሊደረግበትና ሊመራ ይገባል፡፡

4)

ቆጣጣሪዎች ከመድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈፃሚያ የስራ ክፍል ጋር መግባባት ላይ በመድረስ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና በሚሰጡ ተቋማት የሚሰጥ በቂ ሰዓታት ያሉት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና መውሰድ አለበቸው ፡፡

5)

ለም ተቆጣጣሪዎች ከመድኃኒት መልካም አመራረት ስርዓት መስፈርቶች ጋር ተያያዥ የሆነ ተገቢውን የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና ፕሮግራሞችን መውሰድና የስልጠና ሰርተፊኬት ቅጂ ለመደኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ማቅረብ አለባቸው፡፡ የመልካም አመራረት ተቆጣጣሪዎች በዓመት ውስጥ ቢያንስ ለ10 ቀናት ስልጠና ሊወስዱ

manufacturing practice inspector.

8. Without prejudice to sub-article (7) of this article, if it is deemed to be necessary, experts having a minimum of 6 years' experience of working in prequalified and/or good manufacturing practice complied medicine manufacturing companies of Production and Quality Assurance department may be assigned, whenever necessary.
9. Experts having a minimum of 6 years' experience in Regulatory functions at Dossier Evaluation, Medicine Quality Control Laboratory and Medicine Manufacturing Inspection; and having the required qualification, training and competency shall be given priority to be assigned as Lead inspector.
10. International experts from International pharmaceutical Inspection Conventions, prequalification, World Health Organization, Pharmaceutical Inspection Convention, European Medicine Agency and other organizations having the required qualification, experience, and competency as per the above stated provisions may be assigned as inspector whenever necessary.

16. Code of conduct of Inspectors

1) Good manufacturing practice inspector shall behave in an ethical manner and do the task assigned to him/her by the lead good manufacturing practice inspector.
2) Good manufacturing practice inspector shall respect cultural integrity of the country where the facility is situated.
3) Inspectors shall strive to achieve the highest ethical

ይገባል፡፡

6) መልካም አመራረት ስርዓት አረጋጋጭ ቁጥጥር ቡድን መሪ

ሀ) በፋርማሲዉቲክስ ወይም በፋርማሲዉቲካል አናልይሲስ እና ኳሉቲ አሹራንስ ወይም በኢንደስትሪያል ፋርማሲ ወይም ሪጉላቶሪ አፌይርስ ወይም በፋርማሲዉቲካል ማይክሮባዮሎጂ ወይም ፋርማኮሎጂ የተለየ ስፔሻለይዜሽን ያለዉ እና ቢያንስ አስር (10) የውጭ ሀገር የመድኃኒት ፋብሪካዎች ላይ በተለያዩ ጊዜ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ላይ በመሳተፍ ልምድ ያለው እና በቁጥጥር ክህሎቱ አጥጋቢ ውጤት ያስመዘገበመሆን አለበት፡፡

ለ) በፋርማሲ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው በባለስልጣኑ ቴክኒካል የቁጥጥር ስራ ሂደት ውስጥ የሚሰራ እና ቢያንስ አስራ አምስት (15) የውጭ ሀገር የመድኃኒት ፋብሪካዎች ላይ በተለያዩ ጊዜ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ላይ በመሳተፍ ልምድ ያለው እና በቁጥጥር ክህሎቱ አጥጋቢ ውጤት ያስመዘገበመሆን አለበት፡ሆኖም፣ እንደአስፈላጊነቱ በፋርማሲ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው ሆኖ በአስራ አምስት (15) የውጭ ሀገር የመድኃኒት ፋብሪካዎች ላይ በተለያዩ ጊዜ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ላይ በመሳተፍ ልምድ ያለው እና በቁጥጥር ክህሎቱ አጥጋቢ ውጤት ያስመዘገበ በመድኃኒት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ፤ በመድኃኒት ግምገማና ምዝገባ እና የቁጥጥር ስራዎች ላይ ያሉ ባለሙያዎች ከሌሎች ተማሳሳይ የትምርት ዝግጅት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር የቡድን መሪ ሆነው ሊመደቡይችላል

and performance standard in carrying out the inspection activities and shall conduct the inspection with National integrity.

4) Inspectors shall uphold the honor and dignity of a good manufacturing practice, proper time management, on time reporting and good record keeping and avoid association with any enterprise of questionable character or apparent conflict of interest.

5) Any assigned inspector shall not use his/her position for personal gain, and he/she shall not receive presents in any form.

6) Inspectors shall conduct inspection in a manner that assure independence from outside influence and interest that would result in compromise of his ability to render a fair and impartial opinion regarding the inspection conducted.

7) Inspectors shall maintain personal hygiene and dress in respectable attire in accordance with acceptable norms.

8) Without prejudice of the above articles, the inspectors shall be governed by organizational code conduct.

PART FOUR

Application and Program Administration

17. Application procedure

1) Applicant or manufacturer shall submit an application through its Regulatory Information System

7) መልካም አመራረት ሥርዓት ተቆጣጣሪ ሆነው የሚመደቡ ባለሙያዎች በባለስልጣኑ የቁጥጥር ተግባራት ላይ ቢያንስ የሶስት አመት ልምድ ያካበቱ፤ ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ስልጠና ብቃት እና መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው መሆን አለባቸው	2) All correspondence and documents required to be submitted shall be in English. If the document required is not in English, itshall be accompanied by a certified translation.
	18. Program Administration and Management
8) ዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (7) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በቅድመ-ዕውቅና እና/ወይም የመልካም አመራረት ብቃት ማረጋገጫ ባላቸው ማምረቻ ተቋማት ውስጥ የምርት ክፍል እና የጥራት ማረጋገጫ ክፍል ስራ ላይ ቢያንስ የስድስት (6) ዓመት ልምድ ያላቸውና ባለሙያዎች ሊመደቡ ይችላል።	1) Both the local and foreign inspection program shall be managed and directed by the Lead Executive Office. The Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Lead Executive Office shall schedule the inspection trips and provide all the documentations necessary for the program activities. 2) The Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Lead Executive Officeof the Authority shall ensure in advance the presence of any conflict of interest among the assigned inspectors.
9) ስፈሊጊዉን የሙያ ዘርፍ የትምህርት ዝግጅት፣ ተገቢውን ሥልጠናና ብቃት ያለዉ ሆኖ በመድኃኒት ሰነድ ግምገማ፣ በመድኃኒት ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ እና በመደኃኒት ማምረቻ ቁጥጥርስራ ቢያንስ የስድስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው ባለሙያየመልካም አመራረት ስርዓት ተቆጣጣሪ የቡድን መሪ ሆኖ ለመመደብ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡	3) Inspectors and Lead Inspectors shall be nominated by Lead Executiveoffice and appointed by respective Deputy Director General or Director General of the Authority. 4) All local facilities inspection Management, including but not limited to assignment and approval of inspectors, and evaluation of the inspection report shall be handled by the Lead Executive office.
10)	5) Without prejudice to sub-article (4) of this article,

ዓለም ጤና ድርጅት፣ ከዓለም አቀፍ የፋርማሲዩቲካልስ ቁጥጥር ትብብር አባላት ፣ ከአውሮፓውያን መድኃኒት ኤጀንሲ እና ከሌሎች ድርጅቶች በዚህ መመሪያ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት አስፈላጊውን ሙያ ዘርፍ፣ ስልጠናና ብቃት ያለዉ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች እንዲስፈላጊነቱ ተቆጣጣሪ ሆነው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

16. ተቆጣጣሪሥነምግባርደንብ

1) የመልካም አመራረት ስርዓት ተቆጣጣሪ በስነምግባር የታነጸ እና በቡድን መሪው የተሰጠውን ተግባር ማከናወን አለበት፡፡

2) የመልካም አመራረት ስርዓት ተቆጣጣሪ ተቋሙ የሚገኝበትን ሀገር ባህልና እሴቶችን ማክበር አለበት፡፡

3) ተቆጣጣሪዎች ቁጥጥር በሚያከናዉንበት ጊዜ ከፍተኛ ስነምግባርን በመላበስና ከፍ ያለ የአፈፃፀም ደረጃ በማሳካት በታማኝነት የሃገርን ክብር ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

4) ተቆጣጣሪዎች የመልካም አመራረት ስርዓት ቁጥጥር ስነ ምግባርን በመጠበቅ በሰዓቱ ስራ ላይ በመገኘት፣ ሪፖርትን በአግባቡ በመጻፍ፣ በቁጥጥር ወቅት የተገኙትን ችግሮች በአግባቡ በመሰነድ እና ከድርጅቱ ጋር ስራዉ ከሚፈለገዉ ግንኙነት ዉጭ ሌላ ግንኙነትና የጥቅም ግጭት ሊኖራቸዉ አይገባም፡፡

the Lead Executive office may assign appropriate experts from other technical office of the Authority.

6) A maximum of five oversees facilities and not more than three countries shall be assigned for inspection on a single trip.

7) The inspection time schedule shall be decided based on manufacturing complexity and manufactured product properties. The detail inspection time schedule shall be as per attached time schedule of this directive.

19. Inspection planning

1) Earliest inspection application shall be given priority during inspection planning or scheduling.

2) Without prejudice to sub-article (1) of this article, sites whose inspection would be crucial in making an ongoing regulatory decision or meeting an emergency or a public health issue shall be given priority during inspection planning,

20. Classification of deficiency and evaluation of Inspection report

1) Situations involving fraud, misrepresentation or falsification of source data or records linked with medicine manufacturing shall result in a non-compliance rating.

2) Non-compliance shall be noted by inspectors and classified as critical, major, and minor deficiency.

5) ማንኛውም ለቁጥጥር ስራ የተመደበ ተቆጣጣሪ የተሰጠውን ሀላፊነት ለግል ጥቅም ማዋል እና ማንኛውንም አይነት ስጦታ መቀበል የለበትም ፡፡	3) Manufacturers with single critical finding or several major deficiencies (≥6) shall be refused from acceptance for good manufacturing practice Compliance. A letter of non-compliance will be sent to the manufacturer (not more than 20 Ethiopian Business days). However, corrective and preventive action may be required for re-inspection
6) ተቆጣጣሪዎች ከውጫዊ ተጽዕኖ፣ ፍለጎቶች እና አድሎ ነፃ በመሆን ሚዛናዊ እና ገለልተኛ የሆነ ቁጥጥር ማካሄድ ይኖርበቸዋል፡፡	
7) ተቆጣጣሪዎች የግል ንፅህናን የመጠበቅ እና ተቀባይነት ያለው አለባበስ መልበስ አለባቸው፡፡	4) Manufacturers with < 6 major and minor or only minor deficiencies shall be requested to provide corrective and preventive action plan not more than 15 Ethiopian Business days.
8) ከላይ የተጠቀሱት የዚህ አንቀጽ ዴንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተቆጣጣሪዎች በባለስልጣኑ የሥነ ምግባር ደንብ መተዳደር አለበቸው ፡፡	
ክፍል አራት	
ማመልከቻስለማቅረብእናየቁጥጥርመርሀ-ግብር አስተዳደር	5) Submitted Corrective and preventive action plan shall be reviewed and responded to the Manufacturer in not more than 10 Ethiopian Business days. Corrective and preventive action report submitted along with the plan shall be evaluated within the prescribed time
17. **ማመልከቻ ሂደት**	
1) ንኛውም አማልካች ወይንም የመድኃኒት አምራች ማመልካቻውን በባለስልጣኑ የኤላክትሮኒክ የቁጥጥር መረጃ ስርዓት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡	6) Corrective and preventive measures submitted by the manufacturer shall be reviewed (not more than10-Ethiopian Business days) by the inspectors based on the Corrective and preventive action plan and the final Corrective and preventive action evaluation report
2) ለም የሚቀርቡ ደብዳቤዎች እና ሰነዶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆን አለባቸው፡፡.	

የሚፈለገው ሰነድ በእንግሊዝኛ ካልሆነ የሚቀርበው ሰነድ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ ትርጉም ጋር ተያይዞ መሆን አለበት።	including decisions and certificates (Complied facilities) will be sent to the Manufacturers or applicants not more than10-Ethiopian Business days.
18. ፕሮግራም አያያዝና እና አስተዳደር	
1) ሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር የመድኃኒት አምራቾች የቁጥጥር መርሃ ግብር በመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል መያዝና መመራት አለበት፡፡ የመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል የቁጥጥር የጉዞ ዕቅድ ማዘጋጀትና እና ለፕሮግራሙ ትግበራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ሁሉ ማቅረብ አለበት።	7) When there is no deficiency, good manufacturing practice compliance certificate will be submitted to the manufacturer not more than10-Ethiopian Business days after the last date of the inspection
2) ባለስልጣኑ የመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ተቆጣጣሪዎችን ከመመደቡ በፊት የቡድኑ አባላት ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት	8) If a company is not granted a good manufacturing practice compliance certificate, the company can apply for reinspection along with the previous inspection Corrective and preventive action program and report.
3) ቆጣጣሪዎችና የቁጥጥር ቡድን መሪዎች በመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ተለይተው በባለስልጣኑ የመድኃኒት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም በዋና ዳይሬክተር መፅደቅ አለበት።	**21. Inspection Report Writing, Reviewing and Approval Process** 1) The inspection observation shall be recorded on each day after completing the daily inspections according to standard operating procedures for preparing and reviewing the good manufacturing practice inspection report.
4) ሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች ቁጥጥር ፡ የተቆጣጣሪዎችን ምደባና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ጨምሮ፣ የቁጥጥር ሪፖርት ግምገማ በመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ	2) The compiled report shall be submitted to Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Executive Lead Office not more than 10Ethiopian Business days after the last date of inspection 3) A team of experts will review the inspection report within the allotted time frame in accordance with standard operating procedures, as directed by the Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Executive Lead Office of the Authority.

የስራ ክፍል መተዳደር አለበት፡፡	4) The Executive Lead office of the Authority shall make sure that the good manufacturing practice inspection report is sent to the inspected manufacturer not more than 20 Ethiopian Business days after the last date of inspection of the facilities
5) ዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ በመድሃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ከሌሎች የባለሥልጣኑ ቴክኒካል የስራ ክፍሎች ሊመደብ ይችላል።	5) The Inspection report shall be specific and provided with sufficient details in order to allow an independent assessment, comprehension and easy decision making.
6) አንድ የውጭ ሀገር የመልካም አመራረት ቁጥጥር ጉዞ ወቅት የሚታዩ የተቋማት ብዛት ከአምስት መብለጥ የለበትም፥ የሀገራትም ብዛት ከሶስት መብለጥ የለበትም፡፡	6) All the observations that are considered as deficiencies non conformity shall be listed in the report.Each defeciencyincludedin an inspection report should be referenced to the Authority good manufacturing practice guidelines for pharmaceutical products and good manufacturing practice related World Health Organization technical report series . An observation that cannot be reasonably referenced shallnot be listed as a deficiency
7) ቁጥጥር የሚመደበው ጊዜ (መርሀ ግብር) በምርቱ የማምረት ሂደት ውስብስብነት እና በሚመረቱ ምርቶች ባህርይ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት ። ለቁጥጥር የሚመደበው ጊዜ የሚወሰነው በዚህ መመሪያ በተያያዘው የቁጥጥር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መሆን አለበት።	
19. **ቁጥጥር እቅድ ስለማውጣት**	22. **Role of Director General and Deputy Director General in Coordinating Activities**
1) ቅድሚያ የመጣ ማመልካቻ በቁጥጥር እቅድ ወይም መርሃ ግብር ዝግጅት ወቅት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡	1) The inspection activities shall be supervised by medicine sector Deputy Director General of the Authority, whenever necessary, the director General shall be involved infollow up inspection to clear complaints, proposing future strategies, and promote overall regulatory activities, whenever necessary.
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቁጥጥር ስራው በሂደት ላይ ላለ የቁጥጥር ውሳኔ መስጠት ፣ ለድንገተኛ የጤና ችግር ምላሽ	

ለመስጠት ወይም ለሕዝብ የጤና ጥያቄዎች ለመመለስ ወሳኝ ሆኖ ከተገኘ በቁጥጥር ዝግጅት ዕቅድ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

20.

ለ ቁጥጥርግኝቶችአመዳደብናምክረሀሳብአሰጣጥ

1)

ተፈጽበረበሩ ፤ አሳሳች ሆነው የቀረቡ ወይም ሆን ተብሎ በሀሰት የቀረቡ ማናቸውም ከመድኃኒት ማምረት ጋር የተያያዙ መረጃዎች አምራች ድርጅቱን መስፈርቶችን ባለማሟላት ምደባ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ አለበት፡፡

2)

ቆጣጣሪዎች በመልካም አመራረት ስርዓት ቁጥጥር ወቅት የታዩ ክፍተቶችን ግኝቶችን መዝግቦ መያዝና ግኝቶችን ወሳኝ ፡ከፍተኛ ወይም አነስተኛ በማለት መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡

3)

ንድ ወሳኝ ጉድለት የታየበት ወይንም ብዙ ከፍተኛ ጉድለቶች ((≥6) ,የተገኘበት አምራች ድርጀት ከባለስልጣኑ የመልካም አመራራት ስርዓት ፈቃድ እንዳያገኝ ያስከለክላል፡፡ አለማሟለቱንም የሚገልጽ ደብደቤ ከሃያ (20) የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊደርሰው ይገባል፡፡ሆኖም ዳግም ቁጥጥር ለማካሄድ ድርጅቱ የእርምት እርምጃ ዕቅድ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

4)

አምራች ድረጅቱ ከስድስት ያነሰ (< 6)ከፍተኛ ጉድለት እና አነስተኛ ጉድለቶች ብቻ ከተገኙበት

2) Without prejudice to sub-article (1) of this article, Director General and Deputy Director General , the Medicine Sector maytravel to the manufacturing site to supervise, monitor, and have a look at the inspection.

3) Trend reports of successive inspection reports shall be statistically evaluated and consumed for further regulatory measures.

PART FIVE

Administrative Measure and Compliant Handling Procedure

Section-One: Administrative Measure

23. Corrective Notification

1) Corrective notification shall be given by the Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Lead Executive Office when violations are significant enough for the issuance of a corrective notification letter and reasonable expectation exists that the inspector will correct the violation.

2) Corrective measures shall be given by the Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Lead Executive Office in written form immediately after completion of the inspection.

አምራች ከአስራ አምስት የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእርምት እርምጃ ዕቅድ እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት፡፡	**24. Issuance of warning letter** 1) When a minor violation occurs the Deputy Director General, of the Medicine Sector shall give a warning letter to the inspector for the following violations.
5) አምራቹ የተላከ የማስተካከያ እርምጃ ዕቅድ ከአስር(10) የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተገምግሞ ለአመልካቹ መልስ መሰጠት አለበት፡፡ የተለከው የእርምት እርምጃ ሪፖርትና ዕቅድም በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡	a) If the inspector or lead inspector did not submit the inspection report within the time frame b) If the inspector or lead inspector did not follow the inspection report writing procedure
6) አምራቹ የተላኩ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ከአስር (10) የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ የእርምት ዕቀድና የትግበራ ሪፖርት ውጤትን መሰረት በማድረግ በተቆጣጣሪው ተገምግሞ ውሳኔና ሰርቲፊኬት (ተቋሙ ካሚላ) ለአመልካቹ መሰጠት አለበት፡፡	c) If the inspector or lead inspector did not follow the role and responsibilities d) If the inspector or lead inspector did not obey the code of conduct. 2) A warning letter shall be issued within a reasonable period not exceeding ten Business days of the knowledge of the violation by the Deputy Director General, Medicine Sector
7) ንም ዓይነት ጉድለት ያልተገኘበት አምራች የመልካም አመራረት ስርዓት ብቃት ማረጋገጫ ከመጨረሻው የቁጥጥር ስራ ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ ከአስር (10) የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሰጠዋል፡፡	**25. Rigorous disciplinary measure** 1) Any rigorous violation of the inspector shall be considered a rigorous disciplinary violation and shall be governed by the Federal Civil Servants Proclamation No.1064/2017 and take appropriate measures according to the violation of the law.
8) ቋሙ የመልካም አመራረት ስርዓት ብቃት ማረጋገጫ ካልተሰጠው የበፊቱን ግኝት የእርምት እርምጃ መርሀ ግብርና ሪፖርት በማያያዝ ሌላ ቁጥጥር እንዲሰራለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡	2) Notwithstanding sub-article (1) of this article, disciplinary violations shall be presented to the
21.	

ቁጥጥርሪፖርትአፃፃፍ፤ ግምገማናየውሳኔአሰጣጥስርዓት	Authority's Disciplinary Committee based on Federal Government Regulation No. 77/94.
1) ቁጥጥር ግኝቶች የየቀኑን የቁጥጥር ሂደት ካበቃ በኃላ በተቀመጠው የቁጥጥር ሪፖርት አዘጋጃጀትና ግምገማ አንድ ወጥ የአሰራር ስርዓት መሰረት ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡	**26. Administrative measures taken on Manufacturer** 1) Any manufacturer who tries to corrupt or deceive the inspectors in which the authority has evidence of such act, it shall be subjected to rejection of inspection for at least five years.
2) ተቆጣጣሪዎች የተዘጋጀው የቁጥጥር ግኝት ሪፖርት ከቁጥጥር ስራው የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ከአስር (10)የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ ለመድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና የህግ ማስፈጸም የስራ ክፍል ማቅረብ ይገባል፡፡	2) Notwithstanding sub article (1) of this article, any manufacturer who provided false information as evidence of compliance for cgood manufacturing practice shall be rejected and blacklisted for consecutive three years.
3) ባለሙያዎች ቡድን በአንድ ወጥ የአሰራር ስርዓት በተገለጸውና በመድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና የህግ ማስፈጸም የስራ ክፍል በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የቁጥጥር ሪፖርትን በተወሰነለት የግዜ ገደብ ውስጥ ገምግማው ያጠናቅቃሉ፡፡	3) Any manufacturer who became absent deliberately during the inspection process shall be considered as inspected and it shall be rejected. If the manufacturer wants to be inspected in the future, it shall pay the inspection fee based on the information in the Service Fee Regulation.
4) መድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና የህግ ማስፈጸም የስራ ክፍል የቁጥጥር ሪፖርቱ ተቋሙ ቁጥጥር ከተደረገበት ግዜ ጀምሮ ከአስር (10)የኢትዮጵያ የስራ ቀናት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ ለአምራቹ መላኩን ማረጋገጥ አለበት፡፡	4) A manufacturer who showed or tried to show a manufacturing facility other than the site located on the site master file is subjected to rejection.
5) ቁጥጥር ሪፖርቱ በማንኛውም ገለልተኛ አካል ግንዘቤ ሊያዝበት በሚችል፤ ግምገማና ውሳኔ ሊያሰጥ በሚችል መልኩ ግልጽና ዝርዝር መረጃ ያየዘ መሆን አለበት፡፡	**Section-Two፡Complaint Handling Procedure** **27. Complaint related to assignment of inspector** 1) Any candidate inspector shall submit his/her

6) ንደጉድለት የተወሰዱ ምልከታዎች በቁጥጥር ሪፖርቱ መከታት አለባቸው። እንደጉድለት በሪፖርቱ የተካተቱ ምልከታዎች ከባለስልጣኑ የመልካም አመራረት ስርዓት ጋይደላይን እና ከዓለም ጤና ድርጅት የመልካም አመራረት ጋር ተያየዥነት ካላቸው ቴክኒካል ሪፖርቶች መጠቀስ መቻል አለባቸው። ከእዚህ ጋር በምክንያታዊነት የማይጠቀስ ምልከታ እንደጉድለት መዘርዘር ያለበትም።	complaint on assignment of inspectors for good manufacturing practice inspection to the Deputy Director General, Medicine Sector within two business days after the announcement of the inspection team and to the Director General for final decision 2) The complaint prepared in accordance with sub-article (1) of this article shall be in written form and shall provide appropriate documentary evidence and other evidence relevant to the case. 3) Where the complaint fulfills the above-stated requirements, the Deputy Director General, Medicine Sector shall notify its final decision to the complainant not more than 2 business days from the receipt of the complaint.
22. **ራዎችን ከማስተባበር አኳያ የምክትል ዋና ዳይሬክተርና እና የዋና ዳይሬክተር ሚና** 1) **የቁጥጥር ሥራው በዘርፉ የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክትትል ቁጥጥር ወቅት ፣ቅሬታ ለማጣራት ፣የወደፊት ስትራቴጅ ለመጠቆም እና አጠቃላይ የቁጥጥር ሥራዎችን ለማበራታታት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ስራው ላይ መሳተፍ ይኖርበታል።**	4) The decision to the complaint prepared in accordance with sub-article (3) of this article shall, at least, include the reason why the complaint shall not be acceptable for any reasonable ground. 5) The candidate inspector shall request the final decision from the Director General within 2 days, in case, if he/she is not satisfied by the Deputy Director General decision
2) **የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ** (1) **እንደተጠበቀ ሆኖ የመድኃኒት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ዋና ዳይሬክተር በአካል ቦታው ላይ በመገኘት በአምራች ድርጅቱ ላይ የሚካሄደውን የቁጥጥር ስራ ላይ ክትትል ፣ቁጥጥርና፣ የቁጥጥር ምልከታ**	**28. Complaint related to inspection finding and decision** 1) Any manufacturer may appeal against any decision of the Authority within 30 working days from the receipt of an official letter from the Authority.

ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

3) በተከታታይ የተሰሩ የቁጥጥር ስራዎች ሪፖርቶች አዝማሚያዎች በስታቲስቲክስ ቀመር ተገምግመው ለቀጣይ የቁጥጥር እርምጃዎች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

2) The complaint prepared in accordance with sub-article (1) of this article shall, at least state, the Authorities' alleged reason to take the measure, decision of the Authority, reasons of the complainant why he/she believes the measure is unjustifiable or inappropriate and shall be signed and dated by the complainant.

3) The complaint prepared in accordance with sub-article (1) of this article shall be in written form and shall provide appropriate documentary evidence and other evidence relevant to the case.

ክፍል አምስት

አስተዳደራዊ እርምጃ እና ቅሬታ አያያዝ ሥነስርዓት

ንዑስ ክፍል አንድ፡ አስተዳደራዊእርምጃ

23. እርምትማስታወቂያ

1) ተቆጣጣሪው የፈጸመው ጥፋት የእርምት ማስታወቂያ ለመስጠት በቂ ሆኖ ሲገኝ እና ከጥፋት እንደሚታረም በቂ እምነት ሲኖር በመድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ኃላፊ የእርምት ማስታወቂያ ሊሰጠው ይገባል፡፡

2) በመድኃኒት አምራቾች ቁጥጥርና ህግ ማስፈጻሚያ የስራ ክፍል ኃላፊ የሚሰጠው የእርምት ማስታወቂያ በጽሁፍ ሆኖ የቁጥጥር ስራው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

4) Where the complaint fulfills the above-stated requirements, the director general shall submit to the compliant handling committee or other appropriate body

5) The compliant handling committee or other appropriate body shall review the complaint not more than within 60 business days and shall present the decision to the Director General of the Authority

6) The Director General of the Authority shall present the final decision to the manufacturer

7) The manufacturer shall appeal to court in case if still not satisfied by the final decision made by the Director General of the Authority.

24. ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ስለመስጠት

1)

PART SIX

Miscellaneous

ሚከተሉት ቀላል ጥፋቶች/ጥሰቶች ተፈጽመው ሲገኙ የመድኃኒት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለተቆጣጣሪው መስጠት አለበት፡፡

ሀ) ተቆጣጣሪው ወይም መሪ ተቆጣጣሪ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቁጥጥር ሪፖርት ሳያቀርቡ ከቀሩ፤

ለ) ተቆጣጣሪው ወይም መሪ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ሪፖርት አጻጻፍ ስርዓትን ያልተከተለ እንደሆነ፤

ሐ) ተቆጣጣሪው ወይም መሪ ተቆጣጣሪ ሚናቸውን እና ኃላፊነታቸውን ተከትለው በአግባቡ ካልሰሩ፤

መ) ተቆጣጣሪው ወይም መሪ ተቆጣጣሪ የስነ-ምግባር ደንቡን ያላከበሩ እንደሆነ።

2) መድኃኒት ዘርፍ ምክትል ዋና ዲይሬክተር ጥፋቱ እንደተፈጸመ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ከአስር የስራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የማስጠንቀቂያ ደብዲቤውን መስጠት አለበት፡፡

25. ባድየዲሲፕሊንእርምጃ

1) ማንኛቸውም በመልካም ዓመራረት ስርዓት ተቆጣጣሪ በስራ ላይ እያለ የተፈጸሙ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች እንደ ከባድ የዲሲፕሊን ጥሰት ተወስደው በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 የዲሲፕሊን ቅጣት መሠረት መታየት እና ተቆጣጣሪው እንደፈጸመው ጥፋት መጠን ተገቢ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ

29. Confidentiality and conflicts of interest

1) The selected inspector shall declare and sign the conflicts of interest and confidentiality agreement before participating in the good manufacturing practice inspection and shall follow respective standard of operating procedures and directions

2) The inspector shall properly maintain confidential information of the manufacturer unless the manufacturer discloses it.

3) The inspectors shall properly maintain confidential information unless the judiciary body requires it.

30. Record handling

The Medicine Manufacturer Inspection and Enforcement Lead Executive Office shall keep all relevant documents pertaining to good manufacturing practice inspection activities including inspection report for at least until re- inspection done and shall fulfill the requirements on Record Handling Directive.

31. Service Fee

Any person who seeks regulatory service under this directive may be required to pay applicable service in accordance with current rate of service fees regulation.

32. Effective date

This directive shall be effecitive as of the date registered with in the ministry of justice and uploading on the official website of the authority.

ሊወሰድበት ይገባል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ የዲሲፕሊን ክስ በፌደራል መንግስት ሰራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 77/94 መሰረት ባለስልጣኑ ላቋቋመው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተሟልቶ መቅረብ አለበት።

26.

አምራች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ

1)

ንኛውም አምራች ለተቆጣጣሪዎች ሙስና ለመስጠት ወይም ለማታለል ሙከራ ያደረገ እንደሆነና ይህንን ተግባር ስለመፈጸሙ ባለስልጣን መስሪያቤቱ በቂ ማስረጃ ካገኘ ተቋሙ ቢያንስ ለአምስት አመታት የቁጥጥር ስራ ሊከናወንለት አይገባም።

2)

ዚህአንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀሆኖ ማንኛዉምአምራችየመልካምአመራረትስርዓትስለማ ሟላቱ ማረጋገጫየቀረበውመረጃየሀሰትሆኖከተገኘ ጥያቄውውድቅ ተደርጎአምራችድርጅቱቢያንስለተከታታይሶስትአ መታትበጥቁርመዝገብመስፈርአለበት፡፡

3)

ቁጥጥር ስራ በሚከናወንበት ወቅት ሆን ብሎ አምራች ተቋሙ እንዳይታይ የሚጠፋ ማንኛውም አምራች ቁጥጥር እንደተከናወነ ተቆጥሮ የቁጥጥር ይድረግልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረግ አለበት፡፡ በቀጣይ ቁጥጥር እንዲደረግለት ጥያቄ የሚያቀርብ

Heran Gerba

Ethiopian Food and Drug Authority

Director General

Attorney and Consultant Ayalew Bitane

Annex 1:

Table 1: Number of Inspection allocated

Facility Type	**Numberof Daysallocated forInspection**
Facilities having up to four production lines for Re Inspection, New, Renewal, Sudden, Special and Investigation inspectionforEnglishandNonEnglishSpeaking Countries	**3**

ከሆነ በአዲስ መልክ በአገልግሎት ክፍያ ደንብ መሠረት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

4)

ዋናው የሳይት ዋና መዝገብ ላይ ከተገለጸው ውጪ ሌላ የማምረቻ ተቋም ያሳየ ወይም ለማሳየት የሞከረ አምራች የቁጥጥር ይደረግለኝ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ንዑስ ክፍል-ሁለት

የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

27. ከተቆጣጣሪ ምደባ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ቅሬታ

1)

ንኛውም እጩ ተቆጣጣሪ ለመልካም አመራረት ስርዓት ቁጥጥር ስራ የተቆጣጣሪዎች ምደባ ላይ ቅሬታ ካለው የምርመራ ቡድኑ ይፋ ከሆነ በኋላ ባሉት ሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለመድኃኒት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር እና ለዋና ዳይሬክተር ለመጨረሻ ዉሳኔ ማቅረብ አለበት፤

2)

ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ቅሬታ በጽሑፍ የሚቀርብ ሆኖ ተጨማሪ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተገቢ የሰነድ ማስረጃዎችን እና ሌሎች መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፤

3)

ቤቱታ አቅራቢው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ካሟላ የመድኃኒት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክቴር አቤቱታው በደረሰው በ2 ቀናት ውስጥ የመጨረሻውን ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ

Facilities having above five to six productionlines for Re inspection, New, Renewal, Sudden, Special and InvestigationinspectionforEnglishandNon EnglishSpeakingCountries	**4**
Facilities having above Seven and above production lines for Re inspection, New, Renewal, Sudden, Special and Investigation inspection for English- Speaking Countries	**5**
ReportWriting	**1**(For every2.5Facilities)

Attorney and Consultant Ayalew Bitane

ይኖርበታል፤

4) ዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተላለፈው ውሳኔ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነትን ያላገኘ ሲሆን ተቀባይነት ያላገኘው በምን ምክንያት እንደሆነ መጥቀስ ይኖርበታል፤

5) ፌዴ ተቆጣጣሪው የመድኃኒት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተርን ውሳኔ ካልተቀበለዉ እና በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ውሳኔው በደረሰው በ2 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ወደ ባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ለመጨረሻ ዉሳኔ ማቅረብ አለበት፤

28. ከቁጥጥር ግኝት እና ውሳኔ ጋር የተያያዘ ቅሬታ

1) ንኛውም አምራች የባለስልጣኑ ህጋዊ ደብዳቤ ከደረሰው በኃላ ባሉት 30 የሥራ ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ ማናቸውም ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላል፤

2) ዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ቅሬታ ቢያንስ ባለሥልጣኑ እርምጃውን ለመውሰዱ የተጠቀሱ ምክንያቶች፣ የባለስልጣኑ ውሳኔ፣ የአቤቱታ አቅራቢው እርምጃው ምክንያታዊ ያልሆነ ነው ወይም ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ ነው ያለበትን ምክንያት በመጥቀስ እና በአቤቱታ አቅራቢው የተፈረመ እና ቀን የተጻፈበት መሆን ይኖርበታል፤

3)

Attorney and Consultant Ayalew Bitane

ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ቅሬታ በጽሑፍ ሆኖ በተጨማሪ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተገቢ የሰነድ ማስረጃዎችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፤

4)

ቤቱታ አቅራቢው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ካሟላ የባለስልጣኑዋና ዳይሬክተሩ አቤቱታውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ለሌላ አግባብ ላለዉ አካል ማቅረብ ይኖርበታል፤

5)

ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ሌላ አግባብ ያለዉ አካል ቅሬታውን በተቀበለ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ማሳወቅ ይኖርበታል፤

6)

ባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የመጨረሻውን ውሳኔ ለአምራቹ ያሳዉቃል፤

7)

ምራቹ በዋና ዳይሬክተር በተላለፈው የመጨረሻ ውሳኔ ካልተስማማ ቅሬታውን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊል ይችላል፤

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29. ሚስጥር ስለመጠበቅ እና የጥቅም ግጭት ስለማሳወቅ

1)

ቁጥጥር የተመረጡ ተቆጣጣሪዎች የመድኃኒት ተቋማት ቁጥጥር ከማካሄዳቸዉ በፊት ሚስጥር ስለመጠበቅና የጥቅም ግጭት ስምምነት መፈረምና ይፋ ማድረግ እንዲሁም የአሰራር ሂደቶችንና አቅጣጫዎችን መከተል አለባቸው፤

2)

ንኛዉም ተቆጣጣሪ በአምራች ድርጅቱ ይፋ እስካልሆነ ድረስ የአምራች ድርጅቱን ማንኛውንም ሚስጥር መጠበቅ አለበት፤

3)

ቆጣጣሪዎች በማንኛውም በህግ አካላት መረጃዎች እስካልተፈለጉ ድረስ ማንኛውንም የድርጅቱን ሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

30.

ለ ሰነድ አያያዝ

የመድኃኒት ኢንስፔክሽንና ህግ ማስፈጸም መሪ ስራ አስፈጻሚማንኛውንም የመልካም አመራራት ስርዓት የቁጥጥር ስራዎችን እንዲሁም የቁጥጥር ሪፖርት በተመለከተ መረጃዎችን ዳግም ቁጥጥርእስከሚከናወንበት ጊዜ ድረስ የሰነድ አያያዝ መመሪያ በሚያዘዉ መሰረት መያዝ አለበት፡፡

31.

ለ አግልግሎት ክፍያ

ማንኛዉም ሰው የባለስልጣኑን የቁጥጥር አገልግሎት ለማግኘት በቅርብ በወጣ **የአገልግሎት ክፍያ** ደንብ **ስሌት** መሰረት የሚጠየቅን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

32.

መሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድህረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሄራን ገርባ

ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ የምግብ እና መድኃኒት ባለሥልጣን

አባሪ 1፡

ሠንጠረዥ 1፡ ለቁጥጠር ስራ የተመደበ የቀናት ብዛት

የአምራች አይነት	**ለቁጥጥር ስራ የተመደበው የቀናት ብዛት**
አምራቹ እስከ አራት የምርት መስመሮች ያሉት ሆኖ ለአዲስ፣ እድሳት፣ ድንገተኛ፣ ልዩ እና የማጠራት ቁጥጥር የሚከሄድበት የእንግሊዘኛ ተናጋሪ እና የእንግሊዘኛ ተናጋሪ ላልሆኑ ሀገራት ተቋማት	3
አምራቹ ከአምስት እስከ ስድስት የምርት መስመሮች	4

	ያሉት ሆኖ ለአዲስ፣ እድሳት፣ ድንገተኛ፣ ልዩ እና የማጠራት ቁጥጥር የሚከሄድበት የእንግሊዘኛ ተናጋሪ እና የእንግሊዘኛ ተናጋሪ ላልሆኑ ሀገራት ተቋማት		Attorney and Consultant Ayalew Bitane
	አምራቹ ሰባትና ከዚያ በላይ የምርት መስመሮች ያሉት ሆኖ ለአዲስ፣ እድሳት፣ ድንገተኛ፣ ልዩ እና የማጠራት ቁጥጥር የሚከሄድበት የእንግሊዘኛ ተናጋሪ እና የእንግሊዘኛ ተናጋሪ ላልሆኑ ሀገራት ተቋማት	5	
	መ የቁጥጥርሪፖርት ለማዘጋጀት	1 (ለእያንዳንዱ 2.5 ተቋማት)	

Attorney and Consultant Ayalew Bitane